በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ

*መዝ 121፡1*


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

## ኅዳር ፳፫ ቀን ፳፻፪ ዓ.ም.

# ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ

## 1. ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት?

ሀ. ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት፡፡ "…ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች … " ***ማር 11፡1-17፡፡***

ለ. ቤተ ክርስቲያን የስግደት ቤት ናት፤ ለእግዚአብሔር ይሰገድባታል፡፡ "እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ።" ***መዝ 5፡7፡፡***

ሐ. ቤተ ክርስቲያን የመሥዋዕት ቤት ናት፡፡ "ይህ ሕዝብ በእግዚአብሔር ቤት መሥዋዕትን ያቀርብ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ቢወጣ…" ***ቀዳ ነገ 12፡27፡፡***

መ. ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናት ስሙ ይጠራባታል፣ እግዚአብሔር ያድርባታል፣ ተአምራቱን ያሳይባታል፡፡ "ዳዊትም፦ ይህ የእግዚአብሔር ቤት ነው፥ ይህም ለእስራኤል ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነው መሠዊያ ነው አለ።" ***ቀዳ ዜና 22፡1፡፡***

ሠ. ቤተ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር መገናኛ ናት፣ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር ይገናኙባታል፡፡ "በእግዚአብሔር ቤት በመቅደሱ ውስጥ እንገናኝ፡፡" ***ነሀ 6፡10፣ ዘጸ 29፡43፡፡***

ረ. ቤተ ክርስቲያን የበረከት ቤት ናት፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይባርክባታል፡፡ "የጭቃ መሠዊያ ሥራልኝ፥ የሚቃጠለውንና የደኅንነት መሥዋዕትህን በጎችህንም በሬዎችህንም ሠዋበት ስሜን በማሳስብበት ስፍራ ሁሉ ወደ አንተ መጥቼ እባርክሃለሁ።" ***ዘጸ 20፡24፡፡***

ሰ ቤተ ክርስቲያን የንጽህናና የቅድስና ቤት ናት፤ ንጹህና ቅዱስ ኹኖ የሚገባበት የመንፈስ ንጽህናና ቅድስና ያገኝባታል፡፡ "ወደ እግዚአብሔርም የሚቀርቡት ካህናት ደግሞ እግዚአብሔር እንዳያጠፋቸው ራሳቸውን ይቀድሱ አለው።" ***ዘጸ 19፡22፡፡***

## 2. ቤተ ክርስቲያን ለምን ይኬዳል?

ሀ. ለጸሎት፡፡ "አሁንም በዚህ ስፍራ ለሚጸለይ ጸሎት ዓይኖቼ ይገለጣሉ፥ ጆሮቼም ያደምጣሉ።" ***ካል ዜና 7፡15***

ለ. ለስግደት፡፡ "ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ ስምህንም አመሰግናለሁ…።" ***መዝ 137፡2፡፡***

ሐ. ለቅዳሴና ለቁርባን፡፡ "ለአንተ የምስጋና መሥዋዕትን እሠዋለሁ፥ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ። " ***መዝ 116፡17***

መ. ለትምህርት፡፡ "ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኵራብ ገብቶ አስተማረ።" ***ማር 1፡21፡፡***

ሠ. ለምጽዋት፡፡ "ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን አረገ።" ***የሐዋ ሥራ 10፡4፡፡***

ረ. ክርስቲያንነትን በአንድነት (በጉባኤ) ለመግለጽ ለመሳሰለው መንፈሳዊ ጉዳይ ሁሉ፡፡ ***ሥራ 2፡1-35፡፡***

# ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ…

## 3. ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ወይም ለመግባት ቅድመ ዝግጅቱ ምንድር ነው?

ሀ. ያስቀየሙት ሰው ቢኖር ይቅርታ ጠይቆ፡፡

ለ. የተቀየሙት ሰው ቢኖር ይቅር ብሎ ቅሬታን አውርዶ ነው፡፡ ***ማቴ 5፡23-24፡፡*** ቂምና ጥላቻ ይዞ መግባት ይጎዳል እንጂ አይጠቅምም፡፡

ሐ. በስርቆት፣ በቅሚያ፣ በማታለል የወሰዱትን የሰው ገንዘብ መልሶ ነው፡፡ ***ሉቃ 19፡8፡፡***

መ. መጠጥ ጠጥቶ ሰክሮ ቤተ ክርስቲያን መግባት ክልክል ነው፡፡ ***ዘሌዋ 10፡3-10፡፡***

ሠ. የታጠበ ንጹህ ልብስ መልበስ፡፡ "…ዛሬና ነገም ቀድሳቸው፥ ልብሳቸውንም ይጠቡ… "***ዘጸ 19፡10፡፡***

ረ. ሴቶች ከተፈጥሮ ግዳጅ ወንዶችም ዝንየት ያላገኛቸው መሆን፡፡

ሰ የሚሸት ቁስል፣ የሚያነፈርቅ ጉንፋንና ሳል ይዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት አይገባም፡፡

ሸ. ጫማን ማውለቅ፡፡ ***ዘጸ 3፡5፡፤ ኢያሱ 5፡15፡***

ቀ. ልብስን አደግድጎ (መስቀለኛ) አድርጎ መልበስ፡፡ "ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ፡- እነዚህ ነጩን ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ? አለኝ።" ***ራእ 7፡13፡፡***

## 4. ወደ ቤተ ክርስቲያን ከመግባታችን በፊት ምን እናደርጋለን?

- ቤተክርስቲያን ሲገቡ በመጀመሪያ ደጁና ቅኔ ማኅሌቱ መግቢያ ላይ ቆም ብሎ '' ሰላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ዘቀደሰኪ ክርስቶስ በደሙ ንጽሕት'' በማለት በመስቀል ምልክት በማማተብ ለቤተክርስቲያን ይሰገዳል፡፡ "ወደ ቂሣርያም በደረሰ ጊዜ ወጥቶ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ወደ አንጾኪያ ወረደ።'' ***የሐ ሥራ 18፡22፣ ኢሳ 45፡23፤መዝ 80፡9፡፡***

- ቤተ ክርስቲያን በምንገባበት ጊዜ፡-

ሀ. ቅኔ ማኅሌቱን አልፎ ሁለተኛው ክፍል ቅድስቱ መግቢያ ላይ ቆም ብሎ በማማተብ "እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ'' ብሎ አንድ ጊዜ ይሰግዳል፡፡

ለ. የቅድስቱን ክፍል አልፎ እመቅደሱ በር ላይ (ድርገት መውረጃው) በታቦተ-ሕጉ ወይም በታቦተ ምስዋዑ አንፃር ቆሞ በማማተብ "እሰግድ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ '' በማለት ሁለት ጊዜ ይሰገዳል፡፡ እዚህ ላይ ስግደት ሦስት ይሆናል፡፡ ***ዘጸ 33፡10፡፡***

# <u>ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ…</u>

- በአንድ ጊዜ ሦስት መስገድ ለምንድነው ቢባል እግዚአብሔርን በሥጋ፣ በነፍስ በመንፈስም ማምለካችንን ለመግለጽ ነው፡ እነዚህ ሦስት ሕዋሳት በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ተገልጸዋል፡፡ *<u>1ኛ ተሰ 5፡23፡፡</u>*

- በቅዱስቱ መግቢያና በመቅደስ መግቢያ ላይ ሆኖ መስገድ ባያመች ወይም ሁለቱ ክፍሎች (ቅኔ ማኅሌትና ቅድስት) በክልል ቤተ ክርስቲያን ሦስቱንም ስግደት በአንድ ቦታ ላይ ሆኖ መስገድ ይቻላል፡፡

- ይህም ሦስቱ ስግደት በሰንበት እና በሌሎችም ዐበይት በዓላት ሁሉ የማይከለከል የየእለቶች የየሰዓቱ አምልኮተ እግዚአብሔር መግለጫ ነው፡፡

- ቤተክርስቲያን ገብቶ ቀዳሚውን ሥርዓተ ስግደት እንዲህ ካደረሱ በኋላ ተገቢውን ቦታ ይዞ በመቆም የሚጸልዩትን ጸሎት ማድረስ ነው፡፡ ጸሎቱ የግል ከሆነ በለሆሳስ (ድምፅ ሳያሰሙ) በግል መጸለይ፣ የማኅበር ከሆነ የማኅበር ጸሎት ማድረስ ነው፡፡

- በጸሎት ውስጥ ስግደት በሚያወሳበት ክፍል ሁሉ ጸሎቱን እየተናገሩ ይሰገዳል፡፡
- ለፈጣሪ ለእግዚአብሔር የአምልኮ ስግደት ካቀረቡ በኋላ በቤተክርስቲያናችን ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም፣ ለእግዚአብሔር መላእክት፣ ለመስቀለ ክርስቶስ፣ ለቅዱሳን ሰዎች ሁሉ እማሬ ወይም የአክብሮት ስግደት ማቅረብ አለ ይገባልም፡፡ ቅዱሳን የተባሉት ከእመቤታችን ጀምሮ በግብር ስማቸው የተጠቀሱት ናቸው፡፡ *<u>ኢሳ 56፡ 4-7፡፡</u>*

- የእግዚአብሔር መላእክትና ቅዱሳን ሰዎች ፍጹማን ጻድቃን ስለሆኑ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብር አላቸው፤ በረከታቸው ጸሎታቸው ይረዳል፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያን ለቅዱሳን እማሬ የአክብሮት ስግደት ታቀርብላቸዋለች፤ በጸሎታቸው ትማጸናለች፡ ኃይለ እግዚአብሔር ረድኤተ እግዚአብሔር ተገልጾባቸዋል ይገለጽባቸዋልምና፡፡ *<u>ማቴ 10፡40፣ ያዕ 5፡16፡፡</u>*

# <u>ቤተ ክርስቲያን ሊሠራ የማይገባው ተግባር ምንድር ነው?</u>

1. በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ለሥጋዊ ዓላማ ገበያ ማቆም ክልክል ነው፡፡ *<u>ዮሐ2፡16፡፡</u>*
2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክስ መካሰስ መጨቃጨቅ እና ሙግት መሟገት ክልክል ነው፡፡
3. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወግ ማውጋት ተረት መተረት ክልክል ነው፡፡
4. በቤተ ክርስቲያን ጨዋታ መጫወት፣ ቀልድ መቀለድ፣ መዘበት ክልክል ነው፡፡
5. በቤተ ክርስቲያን ሳቅ መሳቅ ሐሜት ማማት አይገባም፡፡
6. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አክታ አክ ማለት ምራቅ መትፋት፣ የአፍንጫን እድገፍ መጣል ክልክል ነው፡፡
7. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለቁርባን ለፈውስ የመጣ ሕመምተና ካልሆነ በቀር መተኛት ክልክል ነው፡፡

- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህን የመሰለ ነውር ተግባርና ከቤት የሚፈጸም ነገርን ሁሉ ማድረግና መናገር አይገባም፡፡
- ክርስቲያን ሁሉ ይህንን አውቆ ወደ ቤተ ክርስቲያን ዘወትር የሚገሰግስ ከሆነ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉት ጊዜ ሁሉ ደስ እያለው ይገሰግሳል፡፡ ካልሆነ ግን ለመሄድ መስነፍ ይገጥማል፡፡ ከላይ በተገለጸው መንገድ ካልሄዱ ድካሙ ሁሉ ከንቱ ይሆናል፡፡

-“በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያመሰግኑ ለተርእዮ አያመስግኑ ልብ በማድረግ ነው እንጂ”

ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 12 ቁጥር 493

ለማናቸውም እርሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ነውና በትምህርቱ ስቦ በረድኤቱ አቅርቦ ሁሉን በማስቻል ደስ እያለን ወደ ቤቱ እንገባ ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን፡፡

ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡